# ሰላም

ሰላም በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል። በገቢ ማነስ፣በወጭ መዛባት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣እንዲሁም በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ በሚፈጠሩ ሁኔታዎች ሁሉ ሰላም ሊጠፋ/ሊሰፍን/ ይችላል። ስለሆነም ሰላም በሰዎች የአኗኗር ዘዴ/ዘየ/ላይ ዘላቂ የመኖር ተስፋ ሊያሳጣ/ሊያስገኝ/ የሚችል ነው።

በመሆኑም ሰላም ማለት የውስጥም የውጭም የሁከት አለመኖር ማለት ነው። ወይም ሰላም ማለት ፍትህ፣ ቀና ፍላጎትና ወንድማማችነትን የመሳሰሉ አዎንታዊ ነገሮች መገኘት ጭምር እንጂ ጭንቀት፣ውዥንብር ወይም ጦርነት የመሳሰሉ አሉታዊ ነገሮች አለመኖር ማለት ብቻ አይደለም። በመሆኑም ሰላም የሚታይ ብጥብጥ አለመኖር ማለትም አይደለም። ሰላም ኃላፊነት መቀበል እና መስዋዕትነትን ይጠይቃል። ፍትሃዊ ሰላም ዘላቂነት የሚኖረው በእያንዳንዱ ግለሰብ ተፈጥሮዓዊ መብቶችና ክብር ላይ የተገነባ ሲሆን ነው። ዜጎች የመናገር፣የማምለክ፣መሪዎቻቸውን የመምረጥ ወይም ያለፍርሃት የመሰብሰብ ነፃነታቸው በተገፈፉ ጊዜ ዘላቂ ሰላም አይኖርም።

ሰላም አሉታዊ ሳላም እና አዎንታዊ ሰላም በመባል በሁለት ይከፈላሉ። አሉታዊ ሰላም በግለሰብ ወይም በቤተሰብ ላይ ግልጽ ሁከት ያለመኖር ውጤት ነው። በሰዎች ህይወት ወይም ንብረት ላይ ቀጥተኛ ጥቃት ሲፈፀም ግልጽ ሁከት ተፈፀመ ይባላል። በግልጽ ሁከት መወገድ ሳቢያ የሚገኘው ሰላም አሉታዊ ሰላም ይባላል። አዎንታዊ ሰላም አዎንታዊ ሰላም የመዋቅራዊ ሁከትያለመኖር ውጤት ነው። መዋቅራዊ ሁከት በአድሎዓዊ ስርዓት ሳቢያ የሚመጣ ድህነት፣ የፍትህ መዛባት፣ ግዙፍ ሙስናዎች በስልጣን መባለጎች፣ ማህይምነትም ቢሆን በአብዛኛው የመዋቅራዊ ሁከት ናቸው። በመዋቅራዊ ሁከት መወገድ ምክንያት የሚገኝ ሰላም ›› አዎንታዊ ሰላም›› ይባላል። በሌላ አነጋገር አዎንታዊ ሰላም የሚሰፍነው ማህበራዊ ፍትህ ሲሰፍን ነው። አዎንታዊ ሰላም ሲኖር ሰዎች ችግሮቻቸውን በድርድር ይፈታሉ። አዎንታዊ ሰላም በማህበራዊ ቡድኖች መካከል ቀና የሆነ መስተጋብር መኖሩ አመልካች ነው። ሌላው የሰላም አይነት ደግሞ አሉታዊ ሰላም እና አምባገነን አገዛዝ ነው። በአንድ አገር ውስጥ አዎንታዊ ሰላም አለ ማለት በዜጎች መካከል መዋቅራዊ መድልዎ አይደረግም ማለት ነው።አዎንታዊ ሰላም የሰፈነበት አገር ህዝብ ከራሱ ጋር የታረቀ ነው።

በዚህ አገር ውስጥ ለዘላቂ ሰላም አስተማማኝ መሰረት ተጥሏል ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር እንችላለን፡፡ ሆኖም ግን አለመግባባቶች ቢነሱ መፍትሄ የሚያገኙበት አሰራር አለ፡፡ አዎንታዊ ሰላም ችግሮች ሲፈጠሩ መፍትሄ እየፈለገላቸው ራሱን ጠብቆ የሚያቆይ ሰላም ነው፡፡ የአዎንታዊ ሰላም መኖር ለዘላቂ ሰላም ዋስትና ነው፡፡ በአንፃሩ አዎንታዊ ሰላም ሳይኖር አሉታዊ ሰላም ሊኖር ይችላል፡፡

በመሆኑም በአማራ ክልል የተከሰተውን የሰላም መደፍረስ ወደ ቀድሞ ገፅታው ለመመለስ መንግስት ከሚመለከተው ህዝብ ጋር ቆም ብሎ በመወያየት ዘላቂ ሰላም ማስፈን አለበት፡፡

<u>ምንጭ</u>

የሰላም ጋዜጠኝነት

በሜቲን ኢሮሲ